

መልክአ ቅዱስ ጊዮርጊስ

በአማርኛ

https://mkidusgeorgeortewahido.com

አንቀጸ ጸሎት።

ልዩ ሦስት የምትሆን ፈጣሪዬ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ ፤ የጥቁሩም የቀዩም ፈጣሪ አንተ እንደ መሆንህ መጠን አቤቱ የጸሎት መጻሕፍት ሁሉ በጥቁርና በቀይ ቀለም አልተጻፉም የሚል የግብዝነት ስሜት እንዳያድርብኝ የቀለም ልዩነት እንዳላደርግ ትዕቢተ ልቡናን አርቅልኝ። ኑፋቄ ጎሊናን አጥፋልኝ። ከሴሰኝነት ከተንኰል ከምቀኝነት ከሐሜትኛለት ከጎሊና ሐኬት ከቁጠኛነት ከትንባሆ ጠጪነት ጫት ከመብላት ከሰካራምነት ክሌብነት ከአታላይነት ከዚህ በላይ ከተጻፉት ወንጀሎችና ከማንኛውም ገቢረ ዓመፃ ሁሉ ነፃ አድርገህ የቸርነትህን አንቀጸ ጸሎት ከፈትልኝ። አቤቱ አንተ በሰጥኽኝ ጸጋ መልካም ሥራ እየሠራሁ የዕለት ምግቤን ስጠኝ። ወደ ፈተና አታግባኝ ከክፉ ሁሉ ጠብቀኝ መንግሥት ያንተ ናት ኃይል ምስጋናም ለዘላለሙ አሜን። ፈጣኑ ጊዮርጊስ ሆይ፤ እኔን አገልጋይህን የጎዘን ማዕበል ባንገላታኝ ጊዜ በፀአዳ ፈረስህ ፈጥነህ ደርሰህ ከጎዘኔ አረጋጋኝ።

እግዚአብሔር ብዙ የሆኑ ጎቡዕና ክሡት ስሞች አሉት ሊቆጠሩና ሊመረመሩ ግን አይቻልም። እግዚአብሔር የጀግኖች አምባ መጠጊያ ነው። እግዚአብሔር ጀግኖችን በሠልፍ የሚያበረታ ነው በእግዚአብሔር ጣዕመ ፍቅር የተጠመደ ሞትን አይፈራም ስለሆነም ነው እነ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ፍቅር የሚያስፈራን ምንድን ነው? ረኃብ

ነው ወይስ ጦርነት እሥራት ነው ወይስ ግርፋት እያሉ እግዚአብሔርን በማመን ከነደደ እሳት ከተሳለ ሰይፍ እየተማገዱ የእግዚአብሔርን መንግሥት ያስተምሩ የነበሩትና ተአምራታዊ ኃይል እየሠሩ የእግዚብሔርን ኃይል በማሳወቅና በማሳመን ምድራዊና ሰማያዊ ክብርን ሊጎናጸፉ የቻሉት (ሮሜ፡፡ከ0) ቅዱስ ጊዮርጊስም ወድ ግብረ ሰምዕትና ተሠምርቶ ትምህርተ ሃይማኖትን በሚሰጥበት ወቅት ከላይ በመጀመሪያው አርእስት እንደ ተጥቀሰው ዘመነ ተጋድሎውን ፈጽሞ እግዚአብሔር በክብር እስከጠራው ድረስ ተቃወሚዎቹ ሥጋውን ቆራርጠው በድንጋይ ቀጥቅጠው በሙቀጫ ወቅጠው ሥጋውን በነፋስ በትነው እፎይታ ለማግኘት በሚሞክሩበት ጊዜ ያለፍራቻ እኔ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ በእግዚአብሔር ኃይል ተነሥቼ የእግዚአብሔርን መንግሥት አስተምራለሁ እያለ በጠላቶቹ ላይ ድልን የተቀዳጀው የእግዚአብሔርን ኅቡዕና ክሡት ስሙን በመጥራት ነው፡፡ እንግዲህ ቅዱስ ጊዮርጊስ የእግዚአብሔርን ህቡዕና ክሡት ስሙን እየጠራ ጠላቶቹን ድል ያደረገበት መልከአ ጊዮርጊስ በአማርኛ ታትሞ ቀርቧልና ከ ዕለት እኪት ከፀበአ ኢጋንንት እንዲሠውራችሁ እግዚአብሔርን በማመን በጸሎቱ ተጠቀሙ፡፡

ተስፋ ገብረ ሥላሴ

ዘብሔረ ቡልጋ

መልክአ ቅዱስ ጊዮርጊስ፡፡

1፤ ለፅንሰትከ ወለልደትከ፡፡

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ መስቀልና በክብር እመቤታችን ድንግል ማርያም ክብረ በዓል ዕለት ለገጠማቸው ክቡር ፅንሰትህና ቡሩክ ልደትህ ሰላም እላለሁ፡፡ ጊዮርጊስ ሆይ ጨካኝና ቁጡ በሆነው በዱድያኖስ አደባባይ ልዩ ልዩ ተአምራትን እንደማድረግህ። በጠዋት በማታ በከንቱ ነገር የሚነሳሱብኝ ጠላቶቼ ሁሉ አንድ አመድ በነው እንደ ጢስ ተነው ይጥፉ፡፡

2፤ ለዝክረ ስምከ።

ጊዮርጊስ ሆይ ለስም አጠራርህና ለተቆላዘመው ለተለሸለሸው የራስ ፀጉርህ ሰላም እላለሁ ብሩህ ወጽዱል ለሆነው ፊትህና ርእስህም ሰላም እላለሁ፡፡ ተአምርኛው ሰማዕት ሆይ አምላካዊ ሥልጣነ ኃይል የተጎናጸፍነህና፡፡ የማዳንከን መስቀል በርሴ ላይ አቀናጅ፡፡ ገድልህ ወንጌልንም በልቦናየ ሠሌዳ ላይ ጻፍ፡፡

3፤ ለቀራንብቲከ።

ጊዮርጊስ ሆይ ዱፉላት ለሆኑት ቀራንብቶችህና ብሩሃት ለሚሆኑ አዕይንቶችህ ሰላም እላለሁ፡፡ የሮማን ከፋይ ለመሰሉት ጉንጮችህና

https://t.me/orthodoxtewahido

አዕዛኖችህም ሰላም እላለሁ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ የሰማዕታት ሁሉ አለቃ፤ እንደመሆንህ ቀድሞ ሰባዓ ነገሥታትን እንደደመሰስካቸው ነበልባላዊ በምትሆን ጸሎትህ ጠላቶቼን ደምስሳቸው፡፡

4፤ ለአእናፊክ።

ጊዮርጊስ ሆይ፤ እንደ ቀይ ሐር ፈትል (ኩበ) ለሚመስሉት ከናፍርህና አዕንፎችህም ሰላም እላለሁ፡፡ እንዲሁም ለፅዕድዋን አስናኖችህና አፍህ ሰላም እላለሁ፡፡ ተአምረኛው ሰማዕት ሆይ፤ ቀድሞ የቢፉሞንን ልጅ ከስዕበተ ኅጢአት ሰውቱነን እንደቀደስከው መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ዕበቃ ዘንድ፤ ሰውነቴን በፍጽምመቀደስ ቀድሰው ከኃጢአት ርኳሰት ንጽህ አድርገኝ፡፡

5፤ ለልሳንከ

ጊዮርጊስ ሆይ፤ የምስጋና አውታረ መዝሙር ለሆኑት ቃልህና አንደበትህ ሰላመ እላለሁ። የምስጋና ቁርባን ለሚነገርባቸው ጉረሮህና እሰትንፋስህም ሰላም እላለሁ፡፡ ተአምር ሠሪው ሰማዕት ሆይ፤ ሙታንን የማንሣት ሥልጣን ተሰጥቶሃልና። አቤቱ ቢሩታዊትን ከአፈ ዘንዶ እንደ አዳንካት እኔንም ከዕለት እኪት ከዘመን መንሱት በጸሎትህ አድነኝ፡፡

6፤ ለከሣድከ።

ጊዮርጊስ ሆይ፤ የመቆረጥና የመመተር ፍርድ ሰተፈረደባቸው መታከፎቶችህና ከሣድህ ሰላም እላለሁ ለተገረፈው ዘባንህና ለተቸነከረው እንግዳዓህም ሰላም እላለሁ፡፡ ኃይሉ ሰማዕት ሆይ፤ እኔን ምስኪኑን አገሊጋይህን ከሃይማኖት መራቆት ከምግባር እጦት ታድነኝ ዘንድ እማልድሃለሁ፡፡ ልብሱ ተጋድሎህን በበጉ (በክርስቶስ) ደም አጥበህ ከአልውያን ቀማኞች ከከሐድያን ወንበዴዎች ጠብቀህ ክብረ ልብስህን በክብር ለመልበስ በቅተሃልና።

7፤ ለሕፅንከ።

ጊዮርጊስ ሆይ ዓሥራወ አዕዳውህን ለሚያንቀላቅሰው ወርችህ ሰላም እላለሁ፡፡ ዳግመኛም የተአምራት መምህር ለሆነው ከንድህና እድ ከዉርናዕህ ሰላም እላለሁ፡፡ ተአምር ሠሪው ሰማዕት ሆይ፤ትግልህ ሕይወት ሥነ ተጋድሎህም መድኃኒት ይሆነኝ ዘንድ ፈጽሜ እማልድሃለሁ፡፡

8፤ ልእመትከ።

ጊዮርጊስ ሆይ፤ ልክብርተ ከንድህና ተባባሪዋ ለሆነችው መዳፍህም ሰላም እላለሁ፡፡ እንዲሁም ለጣቶችህና እንድ ዕንቍ ፊርጥ ለሚያበሩ የእጆችህም አጽፋር ሰላም እላለሁ፡፡ ተአምር ሠሪው ሰማዕት ሆይ፤

https://t.me/onlyorthodoxtewahido

የሰማዕታትና የጭፍሮቻቸው ሁሉ አለቃ ነህና አቤቱ በጥበብህ ከባሕረ ኅዘን አሻግረኝ በባሕር ላይ መሄድ ያልለመድ የባሕርን ጠባይ ሊያውቅ አይችልምና።

9፤ ለገቦከ።

ጊዮርጊስ ሆይ፤ እንደ መስተዋት ለሚያንጸባርቀው ከርስህ ሰላም እላለሁ። ዳግመኛም እንድ ብርሌ ጽሩይ ለሆነው ልቦናህና ለመንትዮች ከ፤ ልያቶችህ ሰላም እላለሁ። አባቴ ጊዮርጊስ ሆይ፤ በሕያው ከርስቶስ ሕያው ነህና አፈሩ ሳሩ ቅጠሉ የመዓዛው ሽታ ልቡናን ወደሚመስጠው አገርህ በአምባላይ ፈረስህ አፈናጠህ ትወስደኝ ዘንድ እማልድሃለሁ።

10፤ለኅሊናከ።

ጊዮርጊስ ሆይ፤ ለውሳጣዊ ገንዘቦችህና ሃሳቦችህም ሁሉ ከቶ ችሎታ ሣይኖረኝ ደፍሬ ሰላም እላለሁ። | ተአምር ሠሪው ሰማዕት ሆይ፤ አዲሱን የወይን ድርሰት በማከታተል አጠጣኝ የኖረ የወይን ጠጅ በኔ ዘንድ አለና እኔም እኮ አዲሱን የምስጋና ውይን ጠጅ አቀርብሃለሁ።

11፤ ለሐከ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ ለተከበሩት አቀያጅችህና ጽኑዕ ለሆነው ወገብህ ሰላም እላለሁ። ከሁለቱ አእጋሮችህም ጋር ለአብራኮችህ ሰላም እላለሁ። ተአምር ሠሪው ሰማአዕት ሆይ፤ የምኩርና የጥበብ መገኛ ነህና ዓለም የጨለማ ጻዕር ጋር በኃይለጸሎትህ ተድላ ደስታ ወዳለበት ወደ ሰማያዊት ጉባዔ አሳርገኝ።

12፤ ለስኳንዊከ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይል፤ ከሁለቱ ተረከዞችህ ጋር ለጫሞችህ ሰላም እላለሁ። እንደከበረ ዕንቍ ለሚያበሩት ለእግር ጽፍሮችህና ጣቶችህም ሰላም እላለሁ። ተአምር ሠሪው ሰማዕት ሆይ፤ ደቁን ምሰሶ በማለምለም ተአምራትህን ገልጸሃልና። ከጽኑ መከራ በጸሎትህ አድነኝ። ሰውን ለሥድቃይ የሚዳርጉ ረኅብ ቸነፈር ከእሱ ይፈልቃሉና።

13፤ ለቆምከ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ የዘምባባ በቀልት ለሚመስለው ሥነ ቆምህ ሰላም እላለሁ። እንዲሁም ለሥነ መልክእህና ለፀዓተ ነፍስህ ሰላም እላለሁ። ተአምር ሠሪው ጊዮርጊስ ሆይ፤ የማስተዋልና የጥበብ መከታ ነህና። ደመና ዝናማትን እንደሚያዘንም ፍጹም የሆነ የሕይወት መንፈስ ከፈጣሪ ዘንድ ላክልኝ።

14፤ ለግንዘት ሥጋከ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ መካነ መቃብሩ በልዳ አገር ለሚገኘው ግንዘተ ሥጋህ ሰላም እላለሁ። ከድንግል ማርያም ፍልሰት ጋር

https://t.me/onlyorthodoxtewahido

ለሚተባበረው ፍልሰትህም ሰላም እላለሁ፡፡ ተአምር ሠሪው ሰማዕት ሆይ፤ የእልፍ አዕላፍ ጭፍራ ኃይል አለቃ እንደመሆንህ መጠን፡፡ ኀብረ መልኳ መስታወት፤ ጠፈሯ መብረቅ ወደ ሆነው ብርሃናዊት አዳራሽህ በረዴትህ ነጥቀህ ወደዚያ አስገባኝ፡፡

15፤ አኮ አኮ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ መጻሕፍትንና ድርሳናትን በማብዛት ሳይሆን በጥቂት ቃላት ብቻ የአፍ ምስጋና አቀርብልሃለሁ፡፡ ተአምር ሠሪው ሰማዕት ሆይ፤ ፈዋሴ ዱያን እንደመሆንህ ከወፍ በሽታ ፈውሰህ የምታድን ነህና ልመናዬንና ጸሎቴን ዘወትር ቸል ሳትል ስማኝ ከሱ በሺ የሚቆጠሩ ልዩ ልዩ ነገሮች ይተላለፋሉና።

16፤ ሰላም ለከ።

የልዳው ጊዮርጊስ ሆይ፤ ለአንተ ሰላምታ ይገባል። ፈረሰኛው ጊዮርጊስ ሆይ፤ ሰላምታ ይገባሃል፡፡ · የተወደደው የልጅዋ የኢየሱስ ክርስቶስና የድንግል ማርያም ዕውነተኛ ምስክር ሆይ፤ ሰላምታ ይገባሃል። የጥበብ መገኛዋ አዳራሽ ሆይ፤ ሰላምታ ላንተ ይገባሃል።

17፤ ሰላም ለከ።

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት ልዩ ልዩ ሥቃዮችን የታገሥህ ጊዮርጊስ ሆይ ሰላምታ ይገባሃል። ሥጋህ ለዓራት ለስድስት ክፍል የተከፋፈለው ጊዮርጊስ ሆይ፤ ናርዶስ ከሚባል የሽቱ አበባ ይልቅ መዓዛህ ይጥመኛልና ሰላምታ ይገባሃል።

18፤ ሰላም ለከ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ ጥበብ አሳደገችህ፤ ማደሪያዋም አደረገችህ፤ በተሰጠህም ቃለ አእምሮ በሴትየዋ ያደረገውን ጸላዔ ሠናይ አስወጥተህ ሰደድክ፡፡ ጊዮርጊስ ሆይ፤ ስለዚህም ስመ መንታ ተባልክ፡፡

19፤ ሰላም ለከ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ የመታሰቢያህ ዜና እጅግ ለሚጥመው ፈጽሞም ለሚያምረው ሰላምታ ይገባል። ጼና መዓዛህም ከዱር አበቦች ሽታ ይልቅ የጣፈጠ ነው፡፡ ጊዮርጊስ ሆይ ዕንቈ ባሕርይ ነህ እኮን፡፡

20፤ ሰላም ለሀገሩ።

ስለቀናችው ሃይማኖት ነፍስህን አሳልፈህ የሰጠህ ጊዮርጊስ ሆይ፤ ሰላምታ ይገባሃል፡፡ ጊዮርጊስ ሆይ፤ በልዩ ልዩ ቅመም ተቀምሞ ከሚሠራ ሽቶ ይልቅ በብዙ ዋጋ የሚገኝ መዓዛው የጣፈጠ ሽቱ አንተ ነህ።

https://t.me/onlyorthodoxtewahido

21፤ሰላም ለከ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ የዘምባባ በቀልት ለሚመስለው ሥነ ቆምህ ሰላም እላለሁ። ሰማዕቱ ጊዮርጊስ ሆይ፤አዕዋፈ ገነት በአንተ ጥላ ሥር ይጠለላሉ። እኒህም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሳምነህ ያጠመቅሃቸው ልብሰ ጥምቀትን የተላበሱ ምዕመን ናቸው።

22፤ ሰላም ለከ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ በአፌ ብቻ ሣይሆን ከልቤ እወድሃለሁና ሰላም እልሃለሁ። ስለዚህ አባት ሆይ፤ ምስጋናዬን ኣታቃልብኝ ተቀብለህ ዋጋዬን አሰጠኝ እንጂ፡ ለእኔ የደሃው ንጹሕ ወርቁ አንተ ጊዮርጊስ ነህና።

23፤ ሰላም ለከ፡

የማርያም አገልጋይዋ ጊዮርጊስ ሆይ፤ ሰላም እልሃለሁ። ከጽጌረዳ አበባ ይልቅ መዓዛ ሃይማኖትህ ለሚጣፍጠው ጊዮርጊስ ሆይ፤ ሰላም እልሃለህይ። የልዳው ኮከብ ጊዮርጊስ ሆይ፤ ሰላም እልሃለሁ።

24፤ ሰላም ለሀገሩ።

ሰላም ለህገሩ፤ሰላም ለደብሩ፤ ሰላም ለመቃብሩ፤ የአምባላይ ፈረሱ እግሩ በቆመበት በዚያ በከናፍሮቹይሳመኝ፤ ወደ ሀገሩም ይውሰደኝ የቅዱስ ጊዮርጊስ ፍቅሩ እጅግ አስጨንቆኛልና፡

25፤ አ፡ፍጡነ ረድኤት።

ለደካማውም ለብርቱውም። ለእርዳታ ፈጥነህ የምትደርስለት ጊዮርጊስ ሆይ፤ ደግነትህ በጐነትህ ከመጠን በላይ ነው እኮን፡ በአማላጅነትህ ለሚተማመኑትም ሁሉ ነፍስ፤ ዋስ ጠበቃ ነህ እኮን። ከቂም በቀል ንጽሕ በመሆን እንደ ክብርት እመቤትህ እንደ ማርያም ርኅሩኅ ልብ ነህና።

26፤ አ፡ፍጡነ ረድኤት።

ጊዮርጊስ ሆይ፤ ከላይ ባለ በሰማይ ከታች ባለ በምድር በብዙ ወገን ለርዳታ ፈጥነህ አደራረስህ የኤፍራታ ርግብ የተባለችው እንደ እመቤትህ ማርያም ነው እኮን። በመሆኑም በእናትህ በቴዎብስትያ ስም እንደስምህ መንታነት የባለ ሟልነት ስምህን ትሰጠኝ ዘንድ ቃል ኪዳን እንድትገባልኝ እማልድሃለሁ።

https://t.me/onlyorthodoxtewahido

27፤ አ፡ፍጡነ ረድኤት።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ አንተን በመታመን ለጠራህ ሁሉ ፈጥነህ ስትደርስለት ከዓውሎ ነፋስ ይልቅ በተፋጠነ ሩጫ ነው እኮን፡፡ ጊዮርጊስ ሆይ፤ የዘወትር ጸሎቴንና የቃሌንም የልመና ጩኸት ትቀበል ዘንድ ለይቅርታና ለምሕረት ፈጥነህ ወደ እኔ ቅረብ፡፡

28፤ አ፡ፍጡነ ረድኤት።

ፈጥኖ ደራሹ ጊዮርጊስ ሆይ፤ ለጠላቴ መሳለቂያ አታድርገኝ ለሚተነኳኮሉኝም መሰደቢያ አታድርገኝ፤ ለክፉ ጐረቤቴም መዘባበቻ አታድርገኝ። | አባቴ ጊዮርጊስ ሆይ፤ የልቤን ኀዘን ስነግርህ ፈጥነህ ጸሎቴን ስማኝ ነገሬንም አድምጠኝ፡፡ ያዘኑትን የምታረጋጋ ሆይ፤ ወደኔ ቅረብ፤ በአጠገቤም ተገኝተህ አለሁልህ በለኝ፡

29፤ አ፡ፍጡነ ረድኤት፡፡

ፈጥኖ ደራሹ ጊዮርጊስ ሆይ፤ አሁንም ለጠላቴ መሣለቂያ አታድርገኝ፡፡ አባቴ ጊዮርጊስ ሆይ፤ የምነግርህን ባለመናቅ ተቀብለህ ልጄ ወዳጄ አገልጋዬ ታዛገፎ ደረስኩልህ በለኝ፡፡

30፤ አ፡ፍጡነ ረድኤት።

ፈጥኖ ደራሹ ጊዮርጊስ ሆይ፤ አንደ ወይን ጠጅ ልብን ደስ የምታሰኝ ነህ እኮን፡፡ ኀዘንን ታስረሳለህና። ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ ልመናችንን ፈጥነህ ስማ፡፡ በባሕር ላይ የምንንሳፈፈውን በየብስ የምንነጉደውን ሁሉ ፈጥነህ እርዳን እምነታችን በአንተ ላይ አድርገናል፡፡

31፤ አ፡ፍጡነ አድኤት።

የእግዚአብሔር እውነተኛ ምስክሩ ፈጥኖ ደራሹ ሰማዕት ኃይሉ ጊዮርጊስ ሆይ፤ በየዕለቱ እርዳታህ አይለየኝ። የዚህ ዓለም ነጋዴ ያለትርፍ መውጣት መውረድ ከንቱ ድካም ነውና፡፡

32፤ አፍጣኒተ ረድኤት።

በችግርና በመከራ ጊዜ ከዓይን ጥቅሻ ይልቅ ለእርዳታ ፈጥንሽ የምትደርሽ ማርያም ሆይ፤በላባ ቤት ሣለ ለያዕቆብ ረዳቱ አንች ነበርሽ እኮን፡፡ ድንግል ሆይ፤ በፍጹም ሃሳቢ በፍጹም ልቦናዋ አንቺን የማትወድ ሰውነት ከወገኖቿ ተለይታ ትጥፋ ትደምሰስ፡፡

https://t.me/orthodoxtewahido

33፤ ምንተኑ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ ሰለ አደረግሽልኝ ውለታ ሁሉ ከቶ ምን ዓይነት ዋጋ ነው የምከፍልሽ፡፡ ቸርነቱን የምትወጂ እመቤቴ ሆይ የኔን ኃጢአት ብትከታተይ ለአንዲት ሰዓት ስንኳ መቆየት ባልቻልኩም ነበርና ቸርነትሽ አማላጅነትሽ ይደረግልኝ።

34፤ ሃይማኖተ ሥሉስ ቅዱስ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ የሥሉስ ቅዱስን ሃይማኖት ስታስተምር ከዓላውያን ነገሥታት ጋር ለሰባት ዓመታት የተጋደልክ ታላቅ አርበኛ ነህ እኮን፡፡ ኃያሉ ጊዮርጊስ ሆይ፤ ድካም የማሰማህ ትጉህ ገበሬ ነህና ዳግመኛ እንዳይጣሉኝ እንዳይተናኰሉኝ ጠላቶቼን እንደ ጢስ አትነህ፤እንደ ጉም አብነህ ፈጥንህ አጥፋቸው፡፡

35፤ ሰብዓተ፡ዓመተ።

ቄራጡን የእግዚአብሔርን ጭፍራ ቅዱስ ጊዮርጊስን ሥጋውን በክፍል በክፍል እየቆራረጡ በእሳት እያቃጠሉ ሐመደ ሥጋውን በነፋስ እየበተኑ አላውያን ነገሥታት ለሰባት ዓመት አሠቃዩት። በዚህም ሁሉ በተቀበለው መከራ በእግዚአብሔር ዘንድ ክብሩ ታላቅ ነው፡፡ በመጽሐፍ እንደተመለከትነውና በጀሮም እንደሰማነው ከሰማዕታት ሁሉ በዓላውያንና በመናፍቃን ዘንድ እጅግ የሚያስፈራ ታላቅ ባለ ግርማ ሰማዕት ነው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም የኢየክርስቶ ክቡር ሰማዕት መሆኑን አምና በፍጹም ክብር ታከብረዋለች፡፡ አቤቱ አምላካችን ሆይ፤ ለታላቁ ሰማዕት ለቅዱስ ጊዮርጊስ በአንተ ዘንድ ባለሟልነትን በመናፍቃንና በአላውያን ዘንድ የመፈራትን ግርማ እንዳጐናጸፈከው ለእኛ የወንጌል ልጆች የምንሆን አገልጋዮችህም በግዙፍ አካልና በረቂቅ መንፈስ ሊተናኰሉን በሚመጡ ጠላቶቻችን ላይ ድል የመንሣትን አክሊል አቀዳጀን አሜን። አቤቱ የጊዮርጊስ አምላክ ሆይ፣ ማረን፤ አቤቱ የጊዮርጊስ አምላክ ሆይ ራራልን፤ አቤቱ የጊዮርጊስ አምላክ ሆይይቅር በለን ለዘላለሙ አሜን። አቡነ ዘበሰማያት።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ፤ የሥሉስ ቅዱስን ሃይማኖት ስታስተምር ከዓላውያን ነገሥታት ጋር ለሰባት ዓመታት የተጋደልክ ታላቅ አርበኛ ነህ እኮን፡፡ ኃያሉ ጊዮርጊስ ሆይ፤ ድካም የማሰማህ ትጉህ ገበሬ ነህና ዳግመኛ እንዳይጣሉኝ እንዳይተናኰሉኝ ጠላቶቼን እንደ ጢስ አትነህ፤እንደ ጉም አብነህ ፈጥንህ አጥፋቸው፡፡

ቄራጡን የእግዚአብሔርን ጭፍራ ቅዱስ ጊዮርጊስን ሥጋውን በክፍል በክፍል እየቆራረጡ በእሳት እያቃጠሉ ሐመደ ሥጋውን በነፋስ እየበተኑ አላውያን ነገሥታት ለሰባት ዓመት አሠቃዩት። በዚህም ሁሉ በተቀበለው መከራ በእግዚአብሔር ዘንድ ክብሩ ታላቅ ነው፡፡ በመጽሐፍ እንደተመለከትነውና በጀሮም እንደሰማነው ከሰማዕታት ሁሉ በዓላውያንና በመናፍቃን ዘንድ እጅግ የሚያስፈራ ታላቅ ባለ ግርማ ሰማዕት ነው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም የኢየክርስቶ ክቡር ሰማዕት መሆኑን አምና በፍጹም ክብር ታከብረዋለች፡፡ አቤቱ አምላካችን ሆይ፤ ለታላቁ ሰማዕት ለቅዱስ ጊዮርጊስ በአንተ ዘንድ ባለሟልነትን በመናፍቃንና በአላውያን ዘንድ የመፈራትን ግርማ እንዳጐናጸፈከው ለእኛ የወንጌል ልጆች የምንሆን አገልጋዮችህም በግዙፍ አካልና በረቂቅ መንፈስ ሊተናኰሉን በሚመጡ ጠላቶቻችን ላይ ድል የመንሣትን አክሊል አቀዳጀን አሜን። አቤቱ የጊዮርጊስ አምላክ ሆይ፣ ማረን፤ አቤቱ የጊዮርጊስ አምላክ ሆይ ራራልን፤ አቤቱ የጊዮርጊስ አምላክ ሆይይቅር በለን ለዘላለሙ አሜን። አቡነ ዘበሰማያት።

Author by pdf : Muse Ambaye
My telegram channel:
https://t.me/onlyorthodoxtewahido
facebook: Muse Ambaye Dagne

https://t.me/onlyorthodoxtewahido